# Learning by Ear 2013

## "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ " "መዘዙን መቀበል"

## EPISODE 15: በሰው ሀገር

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE1: ወ/ሮ ለምለም AND ካሳሁን IN LABORIA**

- **ወይዘሮ ለምለም (F, 40)**
- **ካሳሁን (M, 50)**

**SCENE 2: አልማዝ ARRIVES AT BONGO ACADEMY**

- **ሰብለ (F, 50)**
- **አልማዝ (F, 16)**

**SCENE 3: AT ምኞቴ AND ትዕግስት PLACE**

- **ምኞቴ (M, 35)**
- **ትዕግስት (F, 15)**

**SCENE 4: AT THE MSOTOS’**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**INTRO**

**1. NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ "መዘዙን መቀበል"የተሰኘዉ ሁለተኛዉ ዙር ድራማ ክፍል አስራ አምስት ነዉ። ድራማዉን ለመከታተል በመዘጋጀታችሁ እናመሰግናለን! እስከ አሁን ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ ትዕግስት ከእርሷ በእድሜ በጣም ወደ ሚበልጠው ምኞቴ የተባለው ጓደኛዋ ቤት ጠቅልላ ገብታለች፡

***KW BEGIN***

**2. EPISODE 13, LINE 9:**

<u>ምኞቴ</u>:---- ይኸውልሽ! ትዕግስት፣ ወደ አዲሱ ቤትሽ እንኳን ደህና መጣሽ፡፡ ወይስ የምኞቴ ሚስት ብዬ መጥራት አለብኝ?

***KW END***

**3. NARRATOR:**

ምህረት እና ዳንኤል ተኝተው ምህረት በማርገዟ ምክንያት ሁለቱም ከትምህርት ቤት ታግደዋል። ዳንኤል የመጣዉ በቅርቡ የእርስ በእርስ ጦርነት ከተካሄደበት እና እስከ አሁንም ሁኔታው ካልተረጋጋበት ላቦሪያ ከሚባለው አገር ነው ፡፡ ሀብታም ነጋዴ አባቱን ስልክ ደውሎ ሊያገኛቸዉ አልቻለም፡፡ ሆኖም ከላቦሪያ የመጣች አንዲት ልጅ ግን ዳንኤልን ኪሲምባ ውስጥ ለማግኘት እየጣረች ነዉ። እንደውም ዳንኤል ከትምህርት ቤት ሳይታገድ በፊት ይህችው ልጅ የፍቅር ደብዳቤ ሳይቀር ልካለታለች፡

## 4. EPISODE 12, LINES 22 – 29:

***DAN:*** ሄይ! በለጠ ያንን ደብዳቤ መልስልኝ፡፡

***BIKO:*** *(…)*23 አነብልሀለሁ (…) 28. ***(reads)*** ምን ያህል

እንደምወድድህ ለመግጽ አንድ ነገር እያዘጋጀሁልህ ነው፡፡

አፍቃሪህ- አልማዝ፡፡ (***(normal voice)*** ) አህ-ኦህ… …

***DAN:*** ባክህ አፍህን ዝጋ፣ ትችላለህ፤

## 5. NARRATOR:

የዳንኤል አባት አቶ ካሳሁን ላቦሪያ ውስጥ የማዕድን ኩባንያ አላቸው፡፡ የምህረት ታናናሽ መንታ ወንድሞች፣ ቅዱስ እና ብሩክ፣ አክስታቸው ማዕድን ቁፋሮ ቦታ እንዲሰሩ ብትልካቸውም ለማምለጥ ችለዋል፤

## 6. EPISODE 1, LINE 94:

***BANDA:*** ቅዱስ፣ ስለ ማዕድን ጉዳይ እንድንናገር አይፈቀድልንም!

አክስቴ ለምለም እና ያ ካሳሁን የሚባለው ሰውዬ የነገሩን ያንን ነው፤

## 7. NARRATOR:

ይህ ዛሬ የምንከታተለዉ ድራማ ክፍል “በሰው ሀገር” ይሰኛል። የምንጀምረውም የዳንኤል አባት፣ አቶ ካሳሁንን ከምናገኝበት ከላቦሪያ ነው፡፡ እናም አቶ ካሳሁን ብቻቸውን አይደሉም፤

**SCENE1: ወይዘሮ ለምለም AND ካሳሁን IN LABORIA**

**8. ATMO: COUNTRYSIDE**

**9. SFX: MACHINE GUN FIRE IN THE DISTANCE**

**10.** ወ/ሮ ለምለም: ወታደሮቹ አሁንም ለጥበቃ የሚዘዋወሩ ይመስላል። አቶ ካሳሁን፣ አሁን ከተደበቅንበት ቦታ ፈጥነን መውጣት መቻል ያለብን ይመስለኛል፣

**11.** ካሳሁን: ወ/ሮ ለምለም፣ ያ ጥሩ ሀሳብ አይደለም፣

**12.** ወ/ሮ ለምለም: ግን ሁሉም ሰው አሁን ወደተለመደው ኑሮው ተመልሷል! ወደየስራቸው እየሄዱ በነጻነትም እየተንቀሳቀሱም ነው፣

**13.** ካሳሁን: እኔ እና አንቺ እንደማንኛዉም ሰው አይደለንም። ያንን ደግሞ ታውቂያለሽ። ይህን ህንጻ ለቀቀን በወጣንበት ቅጽበት ይይዙናል። እነዚያን ልጆች ሁሉ በማዕድን ማዉጫ ስፍራዬ ላይ ካገኟቸው በኋላ ፖሊሶቹ በህጻናት ጉልበት ብዝበዛ እና ህጻናትን በማዘዋወር ወንጀል እየፈለጉን ናቸው!

**14.** ወ/ሮ ለምለም: እኔ ግን ከዚህ በላይ እንደዚህ ሆኜ መኖር አልችልም! ይህን ቤት ተመልከት የፈራረሰ ነው። እዚህ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ጥለውት የሄዱት ለዚህ ነው። ተደብቀን ለምን ያህል ጊዜ እንዘልቃለን?

**15.** ካሳሁን: እኛን መፈለጋቸዉን እስኪያቆሙ ድረስ ነዋ!

***KW BEGIN***

**16.** ወ/ሮ ለምለም: እና እንዲህ ሆነን ልንኖር ነው? ከዚህ በኋላ ምግብም እንኳ መግዛት አንችልም።

**17.** ካሳሁን: በትክክል! ባለፉት ሁለት ወራት የነበረሽን ገንዘብ ሁሉ ጨርሰነዋል፡ ፡ እና ወደ ቤት እንዴት ለመመለስ ነዉ ያቀድሽዉ? በእግርሽ? አውሮፕላን በመጥለፍ?

**18.** ወ/ሮ ለምለም: ጦርነቱ ሲያበቃ ገንዘቡን እንደምትመልስልኝ ቃል ገብተህልኝ ነበር፡ ፡

**19.** ካሳሁን: ልክ ነው፡፡ ግን ምን መሰለሽ በባንክ ያስቀመጥኩት ገንዘቤበአጠቃላይ እንዳይንቀሳቀስ ተደርጓል፡፡ ኪሲምባ ላለው ልጄ እንኳን ሰባራ ሳንቲም  መላክ አልቻልኩም፡፡ ዳንኤል  የኪስ ገንዘብ ሳይኖረው ትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት እንደሚኖር አላውቅም፡፡ ለረጅም ጊዜ ድምጹንም አልሰማሁ…

**20.** ወ/ሮ ለምለም: እንደምንም አድርጎ እንደሚወጣው እርግጠኛ ነኝ፡

***KW END***

**21.** ካሳሁን (sighs) ይህ እኔ ላይ ይከሰታል  ብዬ ፈፅሞ ያልጠበቅኩት ነው። እንዴ! ጭራሽ በአንደ ምሽት ከንጉስነት ወደ ተመፅዋችነት፡፡ መቼም ሚስቴ አሁንም ድረስ ለስራ  የሄድኩ ይመስላታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ደግነቱ ሁሉም ነገር ድብልቅልቁ ከመውጣቱ በፊት ወደ ቤተሰቦቿ በመላኬ እድለኛ ነኝ፡

**22.** ወ/ሮ ለምለም: **(trying to calm him down)** ተመልከት፣ አቶ ካሳሁን፣ ነገሮች ቀዝቀዝ ሲሉ የማዕድን ማዉጫ ስራህን መልሰህ እንደምታገኘው እርግጠኛ ነኝ፤

**23.** ካሳሁን: **(laughs bitterly)** እንዴት? ምናልባት ከተዘነጋሽ፤ አዲሱ ወታደራዊ መንግስት እኮ ከእኔ ወገን አይደለም። ከዚህ በኋላ በንግዴ ላይ እንድቀጥል የሚያደርጉኝ ጉቦ ተቀባይ ሚንስቴሮች አይኖሩም። ወ/ሮ ለምለም!ሁሉንም ነገር አጥቻለሁ።

**24.** ወ/ሮ ለምለም: እንደዛ ራስ ወዳድ መሆንህን አቁም። እኔም ብሆን እኮ ሁሉንም ነገሬን አጥቻለሁ። የተረፈኝ ህይወቴ ብቻ ነው! የአንበሳውድርሻ የነበረህ አንተ ነበርክ፤ እንዴ!ሁለቱ የወንድሜ ልጆች ከማዕድን ስፍራው ከጠፉ በኋላ እኮ ወንድሜ ሙላቱ ቢረዳኝ ብዬ ፊቴን ወደእሱ ለማዞር አልደፈርኩም፤

**25.** ካሳሁን: አትጨነቂ፤ ልጆቹ በማዕድን ስፍራው ስለመስራታቸዉ እንደማይናገሩ እርግጠኞች ነን። በጣም ይፈራሉ፤ .

**26.** ወ/ሮ ለምለም: እስከ አሁን ለወላጆቻቸው ምን እንደተናገሩ ማን ያውቃል... ለማንኛውም ለዚህ ያበቃኸኝ አንተ ነህ። አሁን ከዚህ እንድታወጣኝ እና አብረኸኝ እንትሄድ እፈልጋለሁ፤ .

**27.** ካሳሁን: ትንሽ አስቢ እንጂ ወ/ሮ ለምለም። ድንበሩን እንዴት አቋርጠን እንሻገራለን?

**28. ወ/ሮ ለምለም:** **(losing her temper)** ካሳሁን፣ ብቻ ከዚህ አውጣኝ!

**29. ካሳሁን:** **(sighs)**

**30. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: አልማዝ ARRIVES AT BONGO ACADEMY**

**31. ATMO: ሰብለ_ OFFICE ATMO**

**32. SFX: MARKING PAPERS: PEN SCRIBBLING, PAPERS BEING SHUFFLED**

***KW BEGIN***

**33. SFX: PEN PUT DOWN**

**34. ሰብለ:** **(to herself)** ወይኔ አይሆንም!ከ ስብሰባው አርፍጃለሁ። ግን ደግሞ ብዙ የሚሰራ ስራ አለ …

**35. SFX: PHONE BEING PICKED UP, DIALLING NUMBER**

**36. ሰብለ:** ሄሎ፣ ቀለሚ። እየጠበቀኝ ያለሰው ካለ  ነገ እንዲመለስ ንገሪልኝ። **(pause)** ምን?...ማን?...**(pause, remembers)** አዋ እቴ! ከላቦሪያ ለአጭር ጊዜ ቆይታ የመጣችው ተማሪ? እንድትገባ ንገሪያት። የስነ-ስርዓት ኮሚቴውን ደዉይና ምን አልባት ጥቂት ደቂቃ ልዘገይ እንደምችል ንገሪልኝ። አመሰግናለሁ፣

**37. SFX: PHONE REPLACED**

***KW END***

**38. SFX: KNOCK ON THE DOOR**

**39.** ሰብለ: **(calls)** ግቢ

**40. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**41. SFX: FOOTSTEPS - አልማዝ APPROACHES**

**42.** አልማዝ **(confidently)** እንደምንዋሉ፣ አልማዝ ናይዝጊ እባላለሁ፣
ከላቦሪያ ነዉ የመጣሁት። ርዕሰ መምህርት ሰብለ መሆን አለብዎ።
እርሶዎን በማየቴ ደስ ብሎኛል፧

**43.** ሰብለ: አልማዝ፣ ወደ ኪሲምባ እና ቦንጎ አካዳሚ እንኳን ደህና መጣሽ።
ተቀመጪ እባክሽ

**44.** አልማዝ: አመሰግናለሁ፧

**45. SFX: CHAIR PULLED OUT AS SHE SITS**

**46.** ሰብለ: እስኪ ንገሪኝ እቴ፤ አሁን አገራችሁ ሁኔታው ምን ይመስላል፤
እንደከፋ ነው?

**47.** አልማዝ: አሁን እንኳን ስልጣኑን ወታደሮቹ ተቆጣጥረውት በአብዛኛው
አካባቢ ውጊያው ቆሟል። ግን ሁኔታው የተረጋጋ ነው ማለት
አይቻልም። በአሁኑ ወቅት እዚህ ኪሲምባ መሆን በመቻሌ
ቤተሰቦቼ ከስጋት ተርፈዋል፧

**48.** ሰብለ: እስቲ እባክሽ ወረቀቶችሽን ልያቸው?

**49.** አልማዝ: እሺ፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ፡.

**50. SFX: BAG OPENED WITH ZIPPER**

**51. SFX: PAPERS TAKEN OUT AND HANDED OVER**

**52.** አልማዝ: ይኸው !

**53. SFX: PAPER SHUFFLED**

**54.** ሰብለ **(flips papers)** አልማዝ ናይዝጊ ...አስራ ስድስት አመት ...ህምም፡፡ ጥሩ

ነጥብ አለሽ ሳ አልማዝ፡

**55.** አልማዝ: አመሰግናለሁ መምህርት

**56.** ሰብለ: **(reacts to something she’s just read)** እንዴት ደስ የሚል ነው!

እዚህ ጋር የሰለጠንሽ አማካሪ መሆንሽንም ያሳያል፡፡ እዚህ

በወጣት ማዕከሉ ይህንንም ስራ እንደምትቀጥይ እገምታለሁ?

**57.** አልማዝ: አዎ፤ ልክ ነው! እትዬ ሰብለ፤ ሀገሬ ላቦሪያ ውስጥም በወጣት

ማዕከል ውስጥ እሰራ ነበር፤ እና የሚቻል ከሆነ እዚህም

ክህሎቶቼን ለመጠቀም ፈቃደኛ ነኝ፤

***KW BEGIN***

**58.** ሰብለ: ያ ድንቅ ሀሳብ ነው፡፡ ግን እዴት ነው እየተማርሽ ምያንን

ለማከናወንያቀድሽው?

**59.** አልማዝ: በእርሶ ፈቃድ ነው የሚሆነዉ። ከትምህርት በኋላ እና በሳምንት የእረፍት ቀናት በመሄድ መስራት እችላለሁ። በርግጥ የትምህርት ቤቱ ስራ ይቀድማል፡

**60.** ሰብለ: **(impressed)** ነው እንዴ! ደስ ይላል። አልማዝ፣ እዚህ ብዙ እንደምታግዢን አስባለሁ፡

**61.** አልማዝ: አመሰግናለሁ መምህርት። እኔም ያንን እጠብቃለሁ፡

***KW END***

**62.** ሰብለ: በራስ መተማመንሽን ወድጄዋለሁ። መልካም ባህሪ እንደሚኖርሽም ተስፋ አለኝ። እዚህ ቦንጎ አካዳሚ ውስጥ መጥፎ ባህሪያትን ወይም ደንብን የሚጥሱ ተማሪዎችን በቸልታ አናልፍም። እንደውም በቅርቡ በስነ ስርዓት ጉድለት ሶስት ተማሪዎችን አግደናል። መጥፎ ባህሪ ያለሽ ከሆነ እዚህ ለአጭር ጊዜ የልውውጥ ትምህርት መርሃ- ግብር በመምጣትሽ ምክንያትብቻ በተለየ ሁኔታ እንደማላይሽ ላረጋግጥልሽ እወድዳለሁ፡

**63.** አልማዝ: አዎን እትዬ ሰብለ፤ ይገባኛል። አላሳፍሮትም፡

**64.** ሰብለ: መልካም። አሁን አዲሱ ክፍልሽን አሳይሻለሁ፡

**65.** አልማዝ: ኧም-ርዕሰ መምህርት ሰብለ የሆነ ነገር ልጠይቆ እችላለሁ?

**66.** ሰብለ: እሽ ቀጥይ.

**67. አልማዝ:** ዳንኤል ካሳሁንን ያውቁት ይሆን?

**68. ሰብለ:** አዎ፣ በእርግጥ አዉቀዋለሁ፣ ዳንኤል ካባረርናቸው ተማሪዎች መካከል አንዱ ነው፣ .

**69. አልማዝ:** **(surprised)** ምን? ለምን?

**70. ሰብለ:** እንደነገርኩሽ በስነ-ስርዓት ጉድለት ምክንያት ካባረርነዉ ሁለት ወራት ገደማ ሆኗል። እንዴት አወቅሽው?

**71. አልማዝ:** **(stammers)** እርሱ…እኛ …ቤተሰቦቻችን ጓደኛማቾች ናቸው። እኔ…እንዴት እንደሆነ እኔ አላውቅም…

**72. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: AT ምኞቴ AND ትዕግስት PLACE</u>**

**73. ATMO: MUSIC IN THE BACKGROUND**

**74. SFX: CELLPHONE RINGING**

**75. SFX: BEEP AS PHONE IS ANSWERED**

**76. ምኞቴ:** ምኞቴ ነኝ?... **(sweet voice)** ሃሎ!...ልክ ነው፣ የእኔ ጣፋጭ አበባዬ። ታውቂያለሽ፤ አንቺ ለእኔ ያለሽኝ ብቸኛዋ ሴት ነሽ…እንዴ ምን ማለትሽ ነው አደርጋለሁ እንጂ፤ ነገ እንገናኛለን። ያለሽበት ድረስ እመጣለሁ…

**77. SFX: DOOR OPENS**

**78.** ምኞቴ: **(whispers urgently)** በቃ መሄድ አለብኝ፡፡በኋላ እደውልልሻለሁ…

**79. SFX: PHONE DISCONNECTS**

**80.** ምኞቴ: **(overly friendly)** እንዴ ትዕግስት! መጥተሻል ለካ!

**81. SFX: FOOTSTEPS** ትዕግስት **APPROACHING**

**82.** ትዕግስት: እንዴት ነህ ምኞቴ! በስልኩ ከማን ጋር ነበር የምታወራው ? ከእናትህ ጋር?

**83.** ምኞቴ: **(laughs sheepishly)** አዎ እናቴ ነበረች፡፡ ትምህርት እንዴት ነበር?

**84.** ትዕግስት: ጥሩ ነበር፡፡ ግን ትንሽ ደክሞኛል በዛ ላይ ደግሞ እርቦኛል፡ .

**85.** ምኞቴ: እኔም እንደዚያው፡፡ የሆነ የሚጣፍጥ ነገር ለምን አትሰሪልንም?

**86.** ትዕግስት: እም…ጥሩ ነበር፣ ግን ብዙ የእቤት ስራ አለብኝ…

**87.** ምኞቴ: **(a bit annoyed)** እሺ፣ ምግቡን ለማዘጋጀት እኔም አግዝሻለሁ፡፡ ያ ብዙ ነገር እንደሆነ ግን ታውቂያለሽ፣ አይደል?እኔ ብዙውን ጊዜ ምግብ የሚባል ነገር ፈጽሞ አዘጋጅቼ አላውቅም!

**88.** ትዕግስት: አውቃለሁ…አመሰግናለሁ፣ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?

**89.** ምኞቴ: ህምም?

**90.** ትዕግስት: በእውነት ምኞቴ፣ አንተ ጋር ጠቅልዬ በመግባቴ ደስተኛ ነኝ፣

**91. ምኞቴ:** **(pleased with himself) ያን መስማት ያስደስተኛል፡**

**92. SFX: THEY KISS**

**93. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: AT THE MSOTOS'</u>**

**94. ATMO: TANDIKA; INSIDE ምህረት HOUSE, DAYTIME**

**95. ምህረት:** **(crying)**

**96. ቅዱስ:እማ፣ እህቴ ምህረት የምታለቅሰው ለምንድን ነው?**

**97. ወ/ሮ ሉሊት:** **ትምህርት ቤት መመለስ ስለፈለገች ነው ።.**

**98. ቅዱስ:እንዴ! አሁን ብሩክ እና እኔ ትምህርት ቤት አልሄድንም፣ ግን አናለቅስም!**

**99. ወ/ሮ ሉሊት:** **ጥሩ፣ ያ መልካም ነው! እናንተ ወንዶቹ ናችሁ፣ ወንዶች ደግሞ አያለቅሱም፡.**

**100. ቅዱስ:** **አክስቴ ለምለም ያለችውም ያንን ነበር። አልቃሾች አይደለንም!**

**101. ወ/ሮ ሉሊት:** **(strict) የእዚህችን ሴት ስም ደግመህ እንድትጠራብኝ አልፈልግም!**

**(to ምህረት) ምህረት ማልቀስሽን አቁሚ እና የሆነ ነገር ብዪ**

***KW BEGIN***

**102. ምህረት:** **መብላት አልፈልግም፡**

**103.** ወ/ሮ ሉሊት: ሁለት ወራት ሙሉ ይኸው እንዳለቀሰሽ፤ እሺ ታድያ  አሁን ምን ጠቀመሽ?

***KW END***

**104.** ምህረት: አልራበኝም፥ በቃ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ፈልጌ ነዉ።

**105.** ወ/ሮ ሉሊት: ታዲያ እኔ ምን እንዳደርግልሽ ትፈልጊያለሽ? ርዕሰ መምህርቷን አናገርኳት፤ ግን ከዚህ በላይ ልታደርገው የምትችለው ምንም ነገር እንደሌለ ነግራኛለች፥

**106.** ምህረት: **(cries)**

***KW BEGIN***

**107.** ወ/ሮ ሉሊት: የእረፍት ጊዜ ስልጠናዎችን መውሰድ እንደምትችዪ ሀሳብ አቅርባለች፥

**108.** ምህረት: **(still sniffling)** የእረፍት ጊዜ ስልጠና ምንድን ነው?

**109.** ወ/ሮ ሉሊት: ምን ማለቷ እንደሆነ ባይገባኝም...የምትወጂውን፣ የሚስማማሽን የሆነ ነገር ማድረግ፣ መሰልጠን መሰለኝ፥

**110.** ምህረት: **(still crying, but can’t fight laughing)** የሙያ ስልጠና እማ፣ የእረፍት ጊዜ ስልጠና አይደለም!

**111.** ወ/ሮ ሉሊት **(amused)** ምንም ይሁን ምን፣ በያ ትንሽ በተማረችው እናትሽ ላይ በደንብ አላግጪ፡፡ ሁላችንም ብንሆን እንዳንቺ የሀብታም ትምህርት ቤት ለመግባት የፕሬዝዳንቱን የትምህርት ወጪዎች ዕድል አላገኘንም፤

***KW END***

**112.** ቅዱስ: ምህረት ከዚህ በላይ አታልቅሺ፣ ሳድግ ጠንክሬ እሰራና ትምህርት ቤት አስገባሻለሁ፤

**113. THEY LAUGH**

**114.** ምህረት: ውይ ቅዱስዬ አመሰግናለሁ ፣ ትንሹ ወንድሜ! ማን ያውቃል እስኪ ለእዚያ ያድርሰን።

**115. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

በዚሁ የዛሬዉ የበማድመጥ መማር መሰናዶ ይጠናቀቃል። ምህረት ትምህርት ቤት መሄድ ባለመቻሏ ስታዝን አልማዝ በትምህርት ልውውጥ መረሃ ግብር ተማሪነት ቦንጎ አካዳሚ ገብታለች፡፡ በእርግጥም የወንድ ጓደኛዋ ከትምህርት ቤት መታገዱን ከርዕሰ መምህርት ሰብለ ስትሰማ ድንጋጤዋን ለመደበቅ ሞክራለች… ግን ምን አይነት ስሜት እንደተሰማት ማወቅ ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ በድረ-ገጻችን ላይ ያሉትን የቪዲዮ ዘገባዎችዋን ተከታተሉ። የድራማውን ያለፉትክፍሎች ማድመጥ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን <u>**dw.de/lbe**</u> ላይ ታገኙታላችሁ። በፌስቡክ

**አድራሻችንም ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ**

**እስክንገኛኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**